# ዩክሬንን ያየ በእሳት አይጫወትም

ዮናስ 03/19/14

የአየር ንብረቷ ከ0$^{0}$c በታች የሆነችው የዩክሬኗ ኬቭ በቀለም አብዮት እሳት መለብለብ ከጀመረች ቢያንስ ከ3 ወራት በላይ አስቆጠረች። በኬቭ የነፃነት አደባባይ ቅዝቃዜውን ለመቋቋም የወጡ የቢራ ጠርሙሶች በጋዝ እየተሞሉ ወደቦንብነትም መሸጋገር ከጀመሩ በርካታ ቀናት ተቆጥረዋል። መነሻው ደግሞ በቀለም አብዮት  ጥቅሟን ለማስከበር ወደኋላ የማይሉት አሜሪካና ጭፍሮቿ የተጠነሰሰው ዩክሬንን የመጥለፍ ስትራቴጂ ነው።

ከዚህ ቀደም በቡርቱካናማ አብዮት ስያሜ አሜሪካ መራሹ የቀለም አብዮት ቁማርተኞች ቡድን ዩክሬንን ጨምሮ በርከት ያሉ የሩሲያ ሀገረ ግዛቶችን ወደ ራስ ገዝ ሀገርነት ለውጠዋል። የሩሲያ ሁለንተናዊ አቋምና ርዕዮተ አለማዊ ፍልስፍና የገበያ አክራሪ ለሆኑት ሃይሎች ስጋት ነበርና  በእንጭጩ መቀጨት ስለነበረበት ነው ይህ የሆነው። ስለሆነም በውስጥ ተላላኪ ሃይሎችና በኒዮ ሊበራል ሚዲያዎች በመታገዝ በርካታ ረብጣ (ከ60 ሚሊዮን ዶላር በላይ) የተበጀተለት ብርቱካናማው አብዮትም ሩሲያን ገነጣጥሎ ወደ በርካታ ሀገርነት ለወጣት።

በመሰረቱ የውስጥ ተላላኪዎቹ አጀንዳ ግላዊ ጥቅም በመሆኑ ለብርቱካናማው አብዮት በነአሜሪካ የፔርሙዝ አጥሚትና ኬኮች በመታገዝ አደባባይ ሰንብቶ የነበረው ህዝብ እንደህዝብ ያተረፈው አልነበረም።

ሆኖም ባልተቋጨው የቀለም አብዮት ቁማርተኞች ሴራ በወቅቱ ስልጣናቸውን የተነሱት ቪክቶሪያ ያናኮቪች በብርቱካናማው አብዮት ከወረዱ በኋላ ስልጣን ላይ ፊጥ ያለው ተላላኪ ቡድን በሙስና ለመዘፈቁና ሀገሪቱን ቁልቁል ይዞ ለመውረድ ጊዜ አልወሰደበትም። ይህን ጊዜ ታዲያ ለጥቅማቸው ሲሉ የቀለም አብዮቱን በአጋፋሪነት የመሩት ምእራባውያን በሙሰኛው ቡድን አላማቸው  ሊሳካ እንደማይችል ሲረዱት በእነርሱው አስተባባሪነት ምርጫ ተደረገ። በምርጫው አሸንፈው ስልጣንን የተጎናፀፉት ደግሞ በቀለም አብዮቱ  ስልጣናቸውን ተነጥቀው የነበሩት ያናኮቪች መሆናቸው የቁማርተኞቹን ገመና የገለጠ የመጀመሪያው አስገራሚ ሁነት ነው።

ከዚህ ክስተት በኋላ ሁለት ጊዜ በመሳሳት እንዲነቃባቸው ያልፈቀዱት ቁማርተኞች ያደረጉት ቢኖር ህዝብ እንደሚወዳቸውና እንደሚፈልጋቸው በምርጫው ያረጋገጡትን

ያናኮቪች በገበያ አክራሪነት ርዕዮተ አለም ማማለልና ማጥመቅ ነው። እነዚህን ባለጽኑ አቋም መሪ ለማማለልና ለምዕራባውያኑ ተላላኪ ለማድረግም መጀመሪያ ጎረቤታቸውን መጥለፍ አስፈላጊ ነበር። ስለሆነም ከዚሁ አብዮት ከሩሲያ የተፈረካከሱትን የባልቲክ ሀገራት የአውሮፓ ህብረት አባልና የኔቶ አካል ማድረግ የመጀመሪያው ተግባር ሆነ። በመቀጠል ደግሞ ጥያቄው የቀረበው ለያናኮቪችና ዩክሬን ነው። ዳሩ ግን የአውሮፓ ህብረት አባልና የኔቶ አካል የሆኑቱ የባልቲክ ሀገራት እንደምዕራባውያን ሀገራት የእናት ልጅ ሆነው የሚስተናገዱበትና ያሻቸውን የሚወስኑበት መድረክ ሳይሆን በህብረቱ ያላቸው ስፍራ የእንጀራ ልጅነት መሆኑን የተገነዘቡት ያናኮቪች ለጥያቄው አጣዳፊ ምላሽ ከመስጠት ተቆጠቡ።

ከብዙ ድርድር በኋላ በመርህ ደረጃ ዩክሬን የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገር እንድትሆን የተስማሙት ያናኮቪች ይፈርሙት ዘንዳ የቀረበላቸው ሰነድ ግን በወርቅ የተለበጠ ጥይት መሆኑን ሲረዱ ወደኋላ አሉ። ይኸውም 65 በመቶ የሚሆነው የዩክሬን ህዝብ ከሩሲያ ጋር በቋንቋና ባህል አንድ ሆኖ ሳለ የሀገሪቱ የገበያ መዳረሻ ከሆነችው ሩሲያ ጋር የሚያቃቅርና ሩሲያን እንደ ሀገር የምእራባውያን የጥቃት ሰለባ የሚያደርግ ሰነድ መሆኑ ነው ያናኮቪችን ወደኋላ እንዲሉ ያስገደዳቸው።

ስለሆነም የቀለም አብዮቱ ቂማርተኛ ቡድን በፕሬዝዳንቱ በኩል (በአውሮፓ ህብረት ፕሬዝዳንት) ዩክሬንን አወገዘ። ቀጠለናም 20 ሚሊዮን ዶላር ሳምንታዊ በጀት መድቦ ዩክሬናውያንን በኪቭ አደባባይ አሰማራ። የኪቭ ንዳድና ጩኸት የአውሮፓ ህብረት አባል እንሁን ከሚል ጥያቄ ወደ ስልጣን ይልቀቁልን ሲሸጋገር ደገሞ ያናኮቪች አወንታዊ ምላሽ ሰጡ። የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞችን ከመልቀቅ ጀምሮ ህገመንግስቱን እስከ ማሻሻል የሚደርሰውና በቅረቡ ምርጫን ያሰናዳው የያናኮቪች ዴሞክራሲያዊ ውሳኔ ግን ተቀባይነትን አላገኘም። ምክንያቱ ደግሞ የቂማርተኛው ግብ የዩክሬን ህዝብ እንደ ሀገር የመቀጠል ጉዳይ ሳይሆን ሩሲያን ማንኮታኮት ነበርና ነው። በነአሜሪካ የተጠቀለሉ ኬኮች የሚገፋው የዩክሬን ህዝብ ያቀጣጠለው እሳት ያናኮቪችን ለስደት ቢያበቃቸውም በንዳዱ እየተገረፉ ያሉትና እየተሰቃዩ የሚገኙት ዩክሬናውያን ናቸው።

ከዚህ ቀደም ብሎ የቂማርተኞቹን አላማና ግብ በሚገባ የምታውቀውና የምትገነዘበው ሩሲያ ዩክሬን የአውሮፓ ህብረት አባል ሆና የጎን ውጋት ከምትሆንባት እና ይልቁንም ዩክሬንን እንደ ሀገር ተጠቃሚ የሚያደርጋትን አጀንዳ አረቀቀች።

ይኸውም ዩክሬን ኢኮኖሚያዊ አቅሟን የምታጠናክርበትና ከቁማርተኞቹ እዳ መገላገል የሚያስችላትን የ15 ቢሊዮን ዶላር የቦንድ ግዢ ከሩሲያ አገኘች። ዩክሬን ከሩሲያ በምትገዛው የጋዝ ምርትም ላይ ከፍተኛ የዋጋ ቅናሽ በሩሲያ በኩል ተደረገላት። ዳሩ ግን በመርህ ደረጃ ጥቅሙን መሰረት አድርጎ አደባባይ የወጣው ህዝብ በዚህ የሩሲያ አወንታዊ እገዛና ድጋፍ ተታሎ ወደ ቤቱ እንዳይገባ ቁማርተኞቹ ሌላ መላ መቱ። ጽንፈኛ ፖለቲካኞችና አክራሪ ሃይሎች አመጹን እንዲቀላቀሉ አደረጉ። አለም አቀፍ የሚዲያ ዘገባዎች እንዳመለከቱትና የፖለቲካ ተንታኞችም እንደተናገሩት ከሆነ ታጣቂዎች፣ በቡድን የሚያግቱና አልሞ ተኳሾችም በጥቅሉ የአሸባሪነት ባህሪ ያላቸው ቡድኖች አብዮቱን እንዲቀላቀሉ በቁማርተኞቹ በኩል ተሰርቷል።

ማርክስ ፓፓዲለስ የተባሉ የፖለቲካ ፈሎሰፈርና ተንታኝ ጉዳዩን በተመለከተ ሲናገሩ የአሁኑ የኬቭ አዳባባይ ጩኸትና እሳት የአሜሪካው ፔንታጎን በ1992 ያዘጋጀው መመሪያና ሰነድ አካል ነው። ይህ ሰነድ ወደ ላይ እየወጣች ያለችውን ሩሲያ እና ተጽእኖዋን ለመገደብና ለማመናመን የተዘጋጀ ቀመር ነው። ዩክሬን ለሩሲያ መዳከም ጥሩ አማራጭ በመሆኗ ኔቶን እንድትቀላቀል በሰነዱ በግልጽ ተመልክቷል።

46 ሚሊዮን ህዝብ ያላት ዩክሬን፣ የ330 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር ኢኮኖሚ ባለቤት የሆነችው ዩክሬን 500 ሚሊዮን ህዝብ ካለው የህብረቱ የንዳድ ዞን እንድትቀላቀል ለቀረበላት የቁማር ጥያቄም ዩክሬንን ከመፈጥፈጥ የሚያድን ስትራቴጂ የነደፉት ያናኮቪች ከሩሲያም በኩል ይህንኑ ማማለያ የሚያስተነፍስ ምላሽ አግኝተዋል።

ሩሲያን በሚጎዳው ሰነድ ላይ ፈርሙ የተባሉት ያናኮቪች በዋናነት የህዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ስራቸውና ሃላፊነታቸው ነበርና ቢያንስ ዩክሬን ከሩሲያ ልታጣ የምትችላቸውን ነገሮች ሁሉ ታሳቢ ያደረገ የህብረቱ ማካካሻ እንዲደረግላት ጠይቀዋል። ይህን ጥያቄ መመለስ ታዲያ ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጋር በተያያዘና ከነፃ የሰዎች ዝውውር ለማትረፍ አደባባይ የወጡ ሃይሎችን ወደ ቤት ስለሚያስገባ የአውሮፓ ህብረትና ቁማርተኛው ሃይል ለመመለስ አልፈቀደም።

ከላይ በተመለከተው አግባብ የህዝቡ ኑሮ እንዳይስተጓጎልና አመፃው መረን እንዳይለቅም ሰለማዊ ሰልፍን ከሚፈቅደው ማሻሻያ ጀምሮ የያናኮቪች ህገመንግስታዊ የማሻሻያ ውሳኔዎች ሰሚ አጡ። አየሩን ለማሞቅ ወደ ኬቭ አደባባይ ከመጡት የቢራ ጠርሙሶች

ጀምሮ ለበዓላት ማድመቂያ በየሱቁ ተከማችተው የነበሩት ርችቶች ወደ እሳትነት መቀየራቸውን ቀጠሉበት።

ሩሲያ በበኩሏ ለጋራ የንግድ ግንኙነትና ተጠቃሚነት ለዩክሬን ካደረገችው የ15 ቢሊዮን ዶላር የቦንድ ግዢና የጋዝ ዋጋ ቅናሽ ባሻገር ዩክሬንን ጨምሮ ሌሎች ጎረቤት ሀገራትን የሚያስተሳስር ዩሬዥያ የተሰኘ የንግድ ቀጠና መመስረቷን ይፋ አደረገች።

ያም ሆኖ ግን 1 3ኛው ዩክሬናዊ ሩሲያኛን አቀላጥፎ ቢናገርምና ፤ኬቭ የሩሲያ ስልጣኔ መሰረት መሆኗ በሚታወቅበት አለም ቁማርተኛው ሃይል ኬቭ ላይ ወዳጁን ለመትከል 5 ቢሊዮን ዶላር መድቦ ሀገሪቱን በንዳድ መናጡን ተያያዘው። በዚህም ምክንያት ምርጫን የማታውቀው እና ስለሴቶች መብት ደንታ የሌላት ወዳጇን ሳውዲ አረቢያ ለማየት የማትሻው አሜሪካ ስለዩክሬን ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እየታገልኩ ነው ብትል አስቂኝ ይሆናል።

ቫላንቲ ሻኩቪክ የተባሉ የዩክሬን የፖለቲካ ፕሮፌሰርም ጉዳዩን የተመለከተ ማብራሪያ ለመገናኛ ብዙሃኖች ሰጥተዋል ። በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አስርገው ያስገቡትና ሚናቸው ከኬቭ አደባባይ እየገዘፈ የሚገኘው የውጭ ሃይሎች የህዝቡን ፍላጎት እየመረዙት ነው። አክራሪ ማፍያዎችና ቀኝ ዘመም ናዚዎችም ሰልፉን ተቀላቅለዋል። በኢንዱስትሪ ያልበለፀገው ማእከላዊ የዩክሬን ክፍል ምዕራቡን የመጠጋት ፍላጎት ቢኖረውም ከምእራባውያኑ የተዘጋጀውን መርዝ ግን የተረዳ አይመስልም። በኢንደስትሪ የበለጸገው ክፍል ደግሞ የገበያ መዳረሻ ከሆነችን ሩስያ ተጠግተን አብረን ማደግ እንችላላን ሲል ቢጮሁም ሰሚ ማጣቱንም አንዘነጋም።

ስለሆነም ዩክሬን ዛሬ ላይ እንደ ፍየል ቆማ በሚረባረቡባት ብዙ ተኩላዎች ተወጥራ ትገኛለች።

ሁለተኛው የቀለም አብዮት ዩክሬንን እንደ ከዚህ ቀደሙ በጎዳና ላይ ነውጥ ብቻ ሊገድባት አልቻለም። አሁን የሀገሪቱ ሉዓላዊነትም አደጋ ላይ ወድቋል። የቀለም አብዮቱን ቁማርተኞች ገመና ይበልጥ ለመረዳት በቅርብ አመታት ውስጥ የተደረጉትን የአረቡ አለም የጸደይ ክስተቶችና ከሁነቱ በኋላ ዛሬ ግብጽ፣ ሶሪያና ቬንዙዌላን የመሳሰሉት ሀገራት ያሉበትን ሁኔታ ማጤን ያስፈልጋል።

ከድህረ ቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ አለም ዛሬ አንድ ሆናለች። ውስጣዊ ልዩነቶች የሚስተናገዱበት ስርዓትና መንገድም ዛሬ በአለማችን ላይ ተዘርግቷል። ይህ ባለበት ሁኔታ ሀገራት በውስጥ ልዩነት እየታመሱ የሚገኙት ታዲያ ለምንድነው? ብሎ እዚህ ጋር መጠየቅ ተገቢ ይሆናል።

እስከ ዛሬ የውስጥ ልዩነትን መነሻ ያደረገ ትርምስ የተፈጠረባቸውን ሀገራት ወደኋላ መለስ ብለን ስናስታውስ ደግሞ የኒዮ ሊበራል አይዲዮሎጂን አንቀበልም ባሉትና የራሳችን መንገድ አለን ሲሉ በሞገቱት ሀገራት መሆኑን እንገነዘባለን ።

የበሽር አላሳድ ጨካኝነትና የሶሪያውያን ብሶት እንደተጠበቀ ሆኖ የባዝ ፓርቲ እንደ ሪፐብሊካኖቹና ዴሞክራቶቹ የራሱ የሆነ ታሪክና ህልውና ያለው መሆኑና የኒዮ ሊበራሉን ፍልስፍና አልውጥም ለማለት የሚያስችል ህጋዊ መሰረት ያለው መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። የኒዮ ሊበራሉን ኢኮኖሚያዊ ቀመር ቬንዙዌላ ላይ ተክለው ነጻጂን መቀራመት የፈለጉ ሃይሎች እጥረት ፈጥረው ለመሄድ የተገደዱትና የመጨረሻውን ግብ ለመምታት ያልቻሉበት ምክንያት ገዢው ፓርቲ ደጋፊ ስላለውና ፍልስፍናውን የሚቀበል ህዝብ በመኖሩ መሆኑም ሊሰመርበት ይገባል።

የኬቭን አብዮት የቀለም አብዮት ሳይሆን የሞሎቶቭ ኮክቴል አብዮት ነው ሲሉ በስያሜው እንደማይሰማውም ጭምር የሚናገሩ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች፤ የበፊቱም ቢሆን ብርቱካናማ አብዮት ሳይሆን መፈንቅለ መንግስት ነው ሲሉ ይከራከራሉ።በአብዮት ወረዱ የተባሉት ያኑኮቪች ስልጣን ላይ የወጡት በምርጫ አሸንፈው መሆኑንም ለክርክራቸው በምክንያትነት ይጠቅሳሉ።

ለአሁኑ አብዮት በያኑኮቪች ካቢኔ ውስጥ የሚገኙት 6 ጽንፈኛ የቀኝ ፓርቲ ተወካዮችና የኒዮናዚ ፋሽስት አቋም ያላቸው ሚኒስትሮች ጥሩ አጋጣሚ እንደሆኑ የሚገልጹት እነዚህ ተንታኞች፤ በእነዚሁ ጽንፈኞች አማካኝነትም የተወሰኑ ልሂቃን ለኒዮ ሊበራል ሃይሎች እጅ እንዲሰጡና የዴሞክራሲ ክፍተት እንዲፈጥሩ ይደረጋል። በምትኩም ሃብት እንዲያፈሩና የደህንነትና የመከላከያን ተቋም እንዲቆጣጠሩ በማድረግ ዘመቻው ይከፈታል። ዛሬ አለማችን ባፈራችው ቴክኖሎጂ ወደ ነዳጅነት እየተቀየረ በሚገኘው የሼል ቅሪት ክምችት ዩክሬን ግንባር ቀደም መሆኗም እዚህ ጋር ልብ ሊባል ይገባል። መነሻ ነው የተባለው የአውሮፓ ህብረት አባልነትም ቢሆን በህብረቱ ለታቀፉት የምስራቅ አውሮፓ

ሃገራት የሰጠው የእንጀራ ልጅነትን ነው። ስለዚህ ገሚሱ ህብረተሰብ እምቢ ቢል ከራሺያ ጋር ተፈጥሮአዊ (organic) የሆነ ግንኙነት (link) ስላለው በመሆኑ እውነት አለው። 65 በመቶ የሚሆነው ዩክሬናዊ በብርቱካናማው አብዮት (መፈንቅለ መንግስት) ከራሺያ ቢነጠልም ራሺያዊ ማንነቱ ዛሬም አብሮት አለ። ስለሆነም ይህ በዩክሬን ብቻ ሳይሆን በነሶሪያና ሌሎችም ሃገራት እየተደረገ ያለው አብዮት የዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ጥያቄ የወለደው ሳይሆን የአለማዊ ኒዮ ሊበራል ዘመቻ ነው። ስለሆነም በዩክሬን ጉዳይ ራሺያም ይመለከተኛል ብላ ብትነሳ ፍትሃዊና ተገቢነት ያለው ሙግት ነው።

ዩክሬንን የእርስ በርስ ጦርነት ያሰጋታል የሚባለውም ከላይ በተመለከተው መነሻና ሰፊ ቁጥር ያለው ራሺያዊ እና ከናዚ ጋር ተሰልፈው በነበሩ ሃይሎች መካከል የነበረው ቁስል በማመርቀዙ ነው።

በዩክሬን ምድር ግዙፍ የሆነው የራሺያ የጦር ማዕከል ይገኛል። በባህሯም ላይ ቢሆን የራሺያ የደህንነት መቆጣጠሪያ ተገንብቷል። በዩክሬን መናጥና እሳት ተላላኪ ሃይሎች ብቻ ሳይሆኑ ጥቂቱን ህዝብ እያገዘፉና የአብዮቱ አካል አድርገው የሚዘግቡቱ መገናኛ ብዙሃኖችም እጃቸው አለበት ።

እነዚህ ቁማርተኞች ሲቪል ሶሳይቲ የሚባል ማቋመሪያ ፖሊሲን ያነሳሉ። ሲቪል ሶሳይቲ በመሰረቱ ሰፊና ጥልቅ ትርጉም ያለው ማህበረ ሳይንስ ነው። አለም ዛሬ ከሶሻሊስታዊውና ካፒታሊስታዊ ጽንፍ ባሻገርም 3ኛ አማራጭ አለን የሚሉ ሃይሎችንም እያፈራች ነው። ኢትዮጵያንና ሩሲያን የመሰሉ ሃገራት ደግሞ የቀለም አብዮቱን ቁማርተኞች ሴራ ያጤነና የሃገራቸውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ የሲቪል ሶሳይቲ ህግ አላቸው። ህጉ በሀገራዊ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ የባዕዳንን እጅ የሚሰብር ነው። ታዲያ እነዚህ ሃይሎች ህጉን ለማስወገድ የውስጥ ጀሌና ተላላኪዎችን የፖለቲካ፣ የፕሮፓጋንዳና የገንዘብ ትጥቅ አስታጥቀው ከደጅ ያውላሉ። ሙከራወን በተለያየ ደረጃ አይተናል። በምርጫ 97 ወቅት የነበረው |የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን´ አሁን ድረስ በሃይማኖት ስም አክራሪ ሃይሎችን እያሰረገና ጽንፈኛ ፖለቲከኞችንም እያንቀሳቀሰ ነው። ለመናገርና ለመፃፍ ነፃነት ( freedom of expression) እጨነቃለሁ፤ እጠባበለሁ ስትል ኢትዮጵያን የምትከሰውና በጀሌዎቿ በኩል የምታራግበው ሃገረ አሜሪካ ዩክሬንን በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫዋ ላይ ሊዘግቡ የተገኙ የሩሲያና ፀረ ኒዮሊበራል የሆኑ ሚዲያዎች ላይ በሯን ዝግ ማድረጓም ከሰሞኑ መሰማቱ የቁማርተኛውን ገመና ያጋለጠ ሁነት ነው። በጥቅሉ ሲታይ ከሊቢያ

ጀምሮ እስከ ዩክሬን ያለው የቀለም አብዮት መቼቱ ተመሳሳይ ነው። አሁን ግን ማብቂያው ዩክሬን ላይ ይመስላል። በግሎባላይዜሽን ጥናትና ምርምር ውስጥ ከሚነሱ መሰረታዊ ነጥቦች መካከል ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ባሉት 10 አመታት እስከ 1990ዎቹ ማብቂያ ባሉት ጊዜያት የተወሰኑት ናቸው። ከነዚህም ውስጥ የአሜሪካው ፈላስፋና የፖለቲካ ጠበብት ፉኩያማ የፃፈው (The end of history)ይገኝበታል። ፉኩያማ በዚህ መጽሃፉ ማስተላለፍ የፈለገው ገመና ኒዮሊበራል ርዕዮተ አለማዊ ቀመር አለማቀፋዊ ልዕልናን ተጎናጽፋል የሚል ነው። ዛሬ ፀሃይ ቢጠልቅባትም በወቅቱ ፀሃይ የማይጠልቅባት ተብላ የነበረችው ግሬት ብሪቴይን እና እነ አሜሪካ የሚመሩትን ርእዮተ አለም ልዕልናን ማጎናፀፍ ነበር ቀመሩ።

ዳሩ ግን ግሎባላይዜሽን እንደ ሂደት የፈጠረው ትስስር እና ድንበር ዘለሉ የመረጃ ፍሰት እምነታቸውን በመጠነ ኢኮኖሚያዊ አቅም አገራቸውን መምራት የሚያስችል አማራጭ ይዘው ብቅ እንዲሉ ለብዙዎች ሃገራት በር ከፍቷል። አንድ ፓርቲ ተከል የሆነ የእድገት አማራጭም አዋጭነቱ በአለማችን ላይ ታይቷል። ብሪክስ የሚባሉት ሃገራት ብራዚልን ጨምሮ እነ ህንድ ቻይናና ራሺያም ያሉበት ደረጃ የነፉኪያማን ቀመር ውድቅ ያደረገ እውነት ነው። በኢራንም ቢሆን ከኒዩክለሩ ጀርባ ያለው እኔ የሰፈርኩልህን ተቀበል መሆኑም ግልጽ ነው። ያማ ባይሆን ስለሰብአዊ መብትና ስለመፃፍና የመናገር ነጻነት ቀን ከሌት የምታነበንበው የኒዮሊበራሉ ባለቤት የሆነችው አሜሪካ በይፋ የሃገራትን ሉአላዊነት ባልተጻፈረችና ለጋዜጠኞችም ከላይ በተመለከተው አግባብ በሯን ከርችማ ባልዘጋች። ትልቁ ገመና ግን የዴሞክራሲ መገለጫና ጥግ ነው ባሉት ህዝበ ውሳኔ ኮሶቮ ከሰርቢያ በተገነጠለች ሰኣት አጨብጭበውና እኛም እንድናጨበጭብ ወትውተው የነበሩት እነ አሜሪካ ዩክርሚያ በዚሁና የዴሞክራሲ ጥግ ነው ባሉት ህዝበ ውሳኔ ተጠቅማ ወደ ሩሲያ ፌዴሬሽን የሚያስገባትን ውሳኔ በመስጠቷ ልትወገዝ ይገባል መባሉና በተለይ በነ አሜሪካ እየተወገዘች መገኘቷ ነው። ይህ ደግሞ የቀለም አብዮቱ ቁማርተኞች ገመና በሚገባ የተጋለጠበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዘመቻው ማብቂያ ዩክሬን እንደምትሆን አያጠራጥርም ።